SEIU 775 BENEFITS GROUP

ጤና




# 2021 Open Enrollment (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን)

## ጁላይ 1–20 ለግል አገልግሎት ሰጪዎች

### ይህ ፓኬት ለሚከተሉት መረጃዎችን በውስጡ ይዟል፦

- ✓ በጤና መድን ሽፋን ውስጥ ተመዝገቢ የሆኑ እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች።*
- ✓ ለመሳተፍ ብቁ የሆኑ እና የመድን ሽፋን ለማግኘት ማመልከቻ ማስገባት የሚችሉ የእንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች።

*አሁን ላይ የተመዘገቡ የ Aetna አባላት በኦገስት 2021 አዳዲስ መታወቂያ ወረቀቶችን በፖስታ ቤት በኩል ያገኛሉ።

### በOpen Enrollment (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን) ወቅት የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

- ✓ ለጤና ኢንሹራንስ ማመልከቻ ማስገባት (እስካሁን ያልተመዘገቡ ከሆኑ)።
- ✓ በእርስዎ የጥርስ ሕክምና መድን ላይ አማራጭ ለውጦችን ማድረግ (እስካሁን ያልተመዘገቡ ከሆኑ)።
- ✓ ከእርስዎ የጤና መድን ጥቅማ ጥቅሞች እንዴት ሊገኝ የሚችለውን ሁሉ ጥቅም ማግኘት እንደሚችሉ ማወቅ።

### ከ **ጁላይ 20** በፊት ወይም በዚህ ቀን ላይ ኦንላይን ወይም በፖስታ ቤት የእርስዎን የጤና መድን ማመልከቻ ይሙሉ እና መልሰው ያስገቡ።

**አዲስ ለ IPዎች:** በOpen Enrollment (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን) ጊዜ ላይ ብቻ በእርስዎ የመድን ሽፋን ላይ ለውጦችን ማድረግ ይችላሉ። አዲስ ተመዝጋቢዎች ከ አገስት 1 ጀምሮ ሽፋን ማግኘት ይጀምራሉ። አሁን ላይ የተመዘገቡ ከሆነ፣ ምንም ዓይነት እርምጃ ካልተወሰደ አሁን እያገኙ ያሉትን ተመሳሳይ የመድን ሽፋን ማግኘትዎን ይቀጥላሉ።

እስካሁን የጤና መድን ሽፋን ከሌልዎት እና ማመልከቻ ማስገባት የሚፈልጉ ከሆነ፦

- ✓ የጤና መድን ማመልከቻውን ይሙሉት እና ያስገቡት።
- ✓ በወር $25 ይክፈሉ።
- ✓ አገልግሎቱን ለማግኘት ብቁ እንደሆኑ ለመቀጠል በወር 80 ሰዓታት ሥራ መሥራትዎን ይቀጥሉ**
- ✓ በእርስዎ የ Aetna Health Plan /አቴና የጤና መድን/ እና Sav-Rx prescription benefits /ሳቭ-አርኤክስ የታዘዙ መድኃኒቶች መድን/ ተጠቃሚ ይሁኑ!

**የመድን ሽፋን ለማግኘት ብቁ መሆን ስለሚያስችሉ መስፈርቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን የOpen Enrollment (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን) ድረገጽ እዚህ ላይ ይመልከቱ፦ **myseiu.be/oe2021**።

June 15, 2021 3:19 PM

Aetna IP_am-ET.indd 1 15/06/21 15:19

# በእርስዎ ቋንቋ የሚሰጥ መረጃ እና መመሪያ

**Gói này cũng được cung cấp bằng ngôn ngữ của bạn tại địa chỉ myseiu.be/oe2021-vi.** Nếu bạn có câu hỏi, hãy gọi theo số **1-877-606-6705**, từ 8 giờ sáng đến 6 giờ chiều theo giờ Thái Bình Dương, Thứ Hai tới Thứ Sáu.

**此套文档可提供您的语言版本，网址：myseiu.be/oe2021-zh**。如有任何疑问，请致电 **1-877-606-6705** 太平洋时间周一至周五早上 8 点至下午 6 点）。

이 패킷은 **myseiu.be/oe2021-ko** 에서 귀하의 모국어로 제공됩니다. 궁금한 사항은 태평양 표준시 기준으로 월요일부터 금요일까지, 오전 8시부터 오후 6시 사이에 **1-877-606-6705** 로 전화하십시오.

**Este paquete está disponible en su idioma en myseiu.be/oe2021-es.** Si tiene alguna pregunta, llame al **1-877-606-6705**, de lunes a viernes de 8 a. m. a 6 p. m., hora del Pacífico.

**Пакет доступен на вашем языке на сайте: myseiu.be/oe2021-ru.** Для получения дополнительной информации звоните по телефону **1-877-606-6705** с понедельника по пятницу с 8:00 до 18:00 часов (по Тихоокеанскому времени).

**هذه الحزمة متوفرة بلغتك على myseiu.be/oe2021-ar.** إذا كانت لديك أسئلة، اتصل على الرقم **1-877-606-6705** من الساعة 8 صباحا حتى 6 مساء بتوقيت المحيط الهادئ، من الإثنين إلى الجمعة.

ይህ ፓኬት በእርስዎ ቋንቋ **myseiu.be/oe2021-am**. ሊገኝ ይችላል። ጥያቄዎች ካልዎት ወደ **1-877-606-6705**፣ ከ 8 a.m. እስከ 6 p.m. በፓስፊክ ሰዓት አቆጣጠር ከሰኞ እስከ ዓርብ መደወል ይችላሉ።

**Xirmadan iyada oo luuqadaada ah waxaa laga heli karaa bogga intarnetka ee myseiu.be/oe2021-so.** Haddii aad wax su’aalo ah qabto, wac **1-877-606-6705**, 8 a.m. ilaa iyo 6 p.m. Pacific time, Isniin-Jimce.



Aetna IP_am-ET.indd 2 15/06/21 15:19

# ማውጫ

የእርስዎ ፓኬት አንኳር የሆኑ ነጥቦችን ስለ የሚከተሉት ጉዳዮች ያካትታል የእርስዎ የጤና መድን፣ የሕክምና እና የጥርስ ሕክምና የመድን ዕቅዶች አጭር ማጠቃለያዎች እና የተለመዱ ዓይነት የጤና ኢንሹራንስ ውሎች። እስካሁን ካልተመዘገቡ ወይም ቀደም ብለው የተመዘገቡ ሆነው ባልዎት የመድን ዕቅድ ላይ አማራጭ ለውጦችን ያደረጉ ከሆኑ ራስዎት ለመመዝገብ የሚያስፈልግዎትን ቅጾች በተጨማሪ ያገኛሉ።

**አዲስ ለ IPዎች:**

የምዝገባ መስኮትዎ እየተቀየረ ነው! ከ 2021 በፊት፣ የግል አቅራቢዎች (IP) የጤና ሽፋን ላይ መመዝገብ ይችሉ ነበር ወይም መላው አመት ላይ ሽፋንዎን መቀየር ይችሉ ነበር። ከጁላይ 2021 ጀምሮ፣ ጥቅማጥቅም ላይ መመዝገብ የሚችሉት ወይም ሽፋንዎ ላይ ለውጥ ማድረግ የሚችሉት የOpen Enrollment (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን) ጊዜ ላይ ወይም ብቁ የህይወት ጉዳይ ካሎት ብቻ ነው።


**የእኔ ዕቅድ**
ለውጦችን ያድርጉ ወይም አንላይን ይመዝገቡ................ገጽ 4 - 5

**አጠቃላይ ዕይታ**
የጤና እንክብካቤ ዕቅድ ዋና፣ ዋና ነጥቦች....................ገጽ 6 - 7

**ሜዲካል**
የሜዲካል ዕቅድ አጭር ማጠቃለያ ...........................ገጽ 8 - 10

**የጥርስ**
የጥርስ ሕክምና ዕቅድ አጭር ማጠቃለያ .....................ገጽ 11 - 14

**የተለመዱ የኢንሹራንስ ልዩ ቃላት**................ገጽ 15


# እንዴት መመዝገብ ወይም ለውጦችን ማድረግ እንደሚቻል

## አንላይን

ይህን በመጠቀም አንላይን ቅጹን መሙላት ይችላሉ:- *My Plan.* የበለጠ ለማወቅ **myseiu.be/oe-myplan** ን ይጎብኙ።

## መልዕክት ወይም ፋክስ

በጤና መድን ጥቅማ ጥቅም ማመልከቻ ላይ ወደ ተዘረዘረው አድራሻ የእርስዎን ማመልከቻ ይላኩ። የአሜሪካ ፖስታ አገልግሎትን መጠቀም ግዴታ ነው። ወይም ፋክስ ወደ 516-723-7395 ይላኩ።


ለጥያቄዎች፣ ወደ **SEIU 775 Benefits Group Customer Service | 1-877-606-6705 | 8 a.m. - 6 p.m.**፣ ከሰኞ- ዓርብ ይደውሉ | **myseiubenefits.org**

# ይመዝገቡ ወይም ለውጦችን ከየእኔ እቅድ (My Plan) ጋር ያድርጉ!

## ለየእኔ ዕቅድ (My Plan) መለያ ይፍጠሩ

የሚከተሉትን ቅደም ተከተል እርምጃዎች በመከተል እንደ አዲስ ተጠቃሚ ለመመዝገብ ወደ **myseiu.be//oe-myplan** ይሂዱ:-


### እርምጃ 1: እንደ አዲስ ተጠቃሚ ተመዝገብ የሚለውን ይምረጡ።





### እርምጃ 2: አባል መታወቂያ ወይም የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር (SSN) ይውሰዱ።





### እርምጃ 3: ዚፕ ኮድ እና የልደት ቀን ያስገቡ።





### እርምጃ 4: ውሎችን እና አስገዳጅ ሁኔታዎችን ገምግመው መስማማትዎን ያረጋግጡ።





### እርምጃ 5: የተጠቃሚ ስም፣ የይለፍ ቃል እና የደኅንነት ጥያቄውን ይሙሉ።




### እርምጃ 6: የእውቂያ መረጃ ይሙሉ እና መልእክት ልውውጥን ያስቀምጡ።




### እርምጃ 7: ማረጋገጫዎችን ያስቀምጡ።




ጥያቄዎች አልዎት? ወደ **1-877-606-6705**፣ ከ 8 a.m. እስከ 6 p.m. ፓስፊክ ሰዓት አቆጣጠር፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ወደዚህ ይላኩ:- **SEIU775BG-caregiver@magnacare.com**።




Aetna IP_am-ET.indd 4 15/06/21 15:19

## ለመድን ሽፋን ይመዝገቡ

**እርምጃ 1: በመለያ ይግቡ እና የእርስዎን የጤና መድን ሽፋን መረጃ ይመልከቱ ወይም ለመድን ሽፋን ይመዝገቡ።**

ለመመዝገብ ብቁ ከሆኑ፣ በ ምዝገባ ጀምር የሚለው ላይ ጠቅ ለማድረግ የሚያስችል አማራጭ ያገኛሉ።




**እርምጃ 2: My Plan ላይ ያለውን የምዝገባ ሂደት ያሟሉ**

- የእርስዎን ዋና ሥራ ቀጣሪ ይምረጡ። ይህ ከእርስዎ ደመዎዝ ላይ በየወሩ የጣምራ ክፍያውን ድርሻ $25 የሚቆርጠው አሠሪዎ ነው። የእርስዎ ዋና ሥራ ቀጣሪ እርስዎ በየወሩ በሠሩት የሥራ ሰዓታት ብዛት ላይ በመመርኮዝ ወደፊት ሁለተኛ ሥራ ቀጣሪን ለእርስዎ ዳግመኛ ሊመድብ ይችል ይሆናል።
- ለእያንዳንዱ ጥቅማ ጥቅም ለሁለቱም ለኤጀንሲ አገልግሎት ሰጪዎች /Agency Providers (Aps)/ እና ለግለሰብ አገልግሎት ሰጪዎች /Individual Providers (Ips)/ የብቁነት መረጃን ይመለከታሉ።

**እርምጃ 3: እንደሚከተሉት ያሉትን የእርስዎን ምርጫዎች አርትዕ ያድርጓቸው፡-**

- እንዴት እርስዎን ማግኘት እንደሚቻል - በኢሜይል፣ በስልክ ወይም በፖስታ ቤት።
- የእርስዎ ተመራጭ ቋንቋ።

**እርምጃ 4: ለጤና መድን ሽፋን ይመዝገቡ:**

- የሜዲካል መድን ዕቅድ - የእርስዎ መድን ዕቅድ እርስዎ እንደሚኖሩበት ቦታ የሚመረጥ ይሆናል።
- የጥርስ ሕክምና መድን ዕቅድ - የመድን ዕቅዶቹን ያነጻጽሯቸው እና ካሉት የጥርስ ሕክምና መድን ዕቅድ አማራጮች መካከል ይምረጡ።
- እንደ Caregiver Kicks፣ EPIC Hearing እና Ginger የመሳሰሉ ሌሎች የጤና መድን ግብዓቶችንም ማግኘት ይችላሉ።

**እርምጃ 5: የእርስዎን ምርጫዎች ይገምግሟቸው።**

**እርምጃ 6: ምዝገባውን ለማጠናቀቅ የእርስዎን መዳፊት (ማውስ) ወይም የንኪ ሰሌዳ (ተች-ስክሪን) በመጠቀም ስምዎትን ይፈርሙ።**

የማረጋገጫ ማያ ገጽ (ስክሪን) ያያሉ እና ማረጋገጫ ኢሜይል እና ደብዳቤ ይላክልዎታል።

## የእርስዎን የመድን ዕቅድ ይመልከቱ እና ለውጦችን ያድርጉበት

**እርምጃ 1: የእርስዎን የመድን ሽፋን ለማየት ወይም ለውጦችን ለማድረግ ወደ My Plan በመለያ ይግቡ።**

**እርምጃ 2: የሚከተሉትን ለማድረግ ከላይ በግራ ጥግ ያለውን የምናሌ /ሜኑ/ አዶውን ይጠቀሙ፡-**

- የእርስዎን የመድን ሽፋን አጭር ማጠቃለያ ማግኘት
- የእርስዎን ብቁነት እና የጥቅማ ጥቅም መረጃ መመልከት
- የእርስዎን የጥርስ ሕክምና የመድን ዕቅድ መለወጥ
- የእርስዎን የሥራ ሰዓታት ማየት።
- የራስ ክፍያዎችን መፈጸም እና ተጨማሪ ነገሮችን ማድረግ!

**በቀላሉ My Planን ለመጠቀም በእርስዎ ስማርት ስልክ ልይ የ MyCreateHealth ሞባይል መተግበሪያን ያውርዱ።**

የ MyCreateHealth ሞባይል መተግበሪያ በእርስዎ iPhone ላይ በ App Store ወይም በእርስዎ Android ስልክ ላይ በ Google Play Store ላይ ይገኛል።




GET IT ON Google Play

Download on the App Store

# የጤና እንክብካቤ ዕቅድ ዋና፣ ዋና ነጥቦች

## በወር **$25** ብቻ በመክፈል ከፍተኛ ጥራት ያለው የጤና እና የጥርስ ሕክምና የመድን ሽፋን ያግኙ

### የእርስዎ መድን ሽፋን የሚከተሉትን ጥቅማ ጥቅሞች ያካትታል፡

- በነጻ በሐኪም መታየት
- ሜዲካል
- ኦርቶዶንቲያ
- የጥርስ ሕክምና
- የማየት ችሎታ
- መስማት ችሎታ
- መካንነት
- በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት
- የስሜት ድጋፍ

## ከእርስዎ መድን ሽፋን ማግኘት የሚችሉትን ሁሉ ጥቅም ያግኙ

### የሚወዱትን ዶክተር ያግኙ

እንክብካቤ ከራስዎ ይጀምራል። በጣምራ ክፍያ ሊመረምርዎትና ሊያክምዎት የሚችል ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ዶክተር በመምረጥ ከሚያምኑት ዶክተር ጋር ጥሩ ግንኙነትን ያዳብሩ። ይህንን ዶክተር ለአጠቃላይ የጤንነት ማረጋገጫ ጉብኝቶች ዝምብለው ሊያዩት፣ ወይም ከታመሙ ወይም ወደ ስፔሺያሊስት ሪፌራል ካስፈለግዎት ሊያገኙት ይችላሉ።

በ Aetna የድር ጣቢያ በኩል ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ዶክተርን መመደብ ይችላሉ። ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ዶክተር መምረጥ እና መመደብ ፈጣን እና ቀላል ነው። መለያ መፍጠር ላይ ወይም ዶክተር ማግኘት ላይ እገዛ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡- **myseiu.be/oe-doctor**።

### የጤና እንክብካቤ በየትኛውም ቦታ ላይ ማግኘት

ከእርስዎ የመድን ሽፋን ጋር ምቹ፣ ነጻ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ከየትኛውም ቦታ ላይ ሆነው በአካል ተገኝቶ ከመታከም በተጨማሪ - በስልክ፣ በታብሌት፣ በኮምፒውተር አገልግሎት ያገኛሉ። ከፍተኛ ጥራት ያለው ግላዊነት የተላበሰ እንክብካቤ፣ ለደኅንነት አስተማማኝ እና ምቹ በሐኪም መታየቶችን እና የቴክኖሎጂ አማራጮችን በማግኘት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ። ለተጨማሪ **myseiu.be/ha-2021** ን ይመልከቱ።

## ለእርስዎ ብቻ ይበልጥ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ጥቅማ ጥቅሞች

### ለራስ እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡- የሥነ ስሜት ጤና ጥቅማ ጥቅሞች

የሥነ ስሜት ጤና ልክ እንደ አካላዊ ጤናዎ ሁሉ አስፈላጊ ነው። የመድን ሽፋኑ ሳይኮቴራፒ፣ መድኃኒት፣ በቡድን የሚሰጥ ቴራፒ እና ተጨማሪ እና አማራጭ መድኃኒቶችንም ጭምር ያካትታል፡-

- በነጻ እና ለደኅንነት አስተማማኝ በሆነ የጽሑፍ መልእክት መላላክ በኩል ለእርስዎ ምክር እና እገዛ መስጠት ከሚችል ኤክስፐርት አሠልጣኝ ጋር የ Ginger መተግበሪያ ቀላል ያደርግልዎታል። እዚህ ላይ የበለጠ ይረዱ፡- **myseiu.be/oe-ginger**።
- ምቹ ከሆነ የ8-ሳምንት የስልክ/ቪዲዮ የምክር አገልግሎት እና የሥልጠና ፕሮግራም ጋር ከእርስዎ ፕሮግራም ጋር የሚስማማ እውነተኛ እገዛ ለማግኘት በ Aetna የቀረበው AbleTo Support። የበለጠ ለመረዳት ወደዚህ ይደውሉ፡- **1-855-773-2354**።
- በ Resource Finder* አማካኝነት የግል ሕይወት እገዛ። በ Resource Finder በኩል፣ ወደ ሥነ ስሜት የጤና ግብዓቶች፣ የሕፃን እንክብካቤ፣ ሕጋዊ እገዛ እና ተጨማሪ ነገሮች መዳረሻን ማግኘት ይችላሉ። የበለጠ ለማወቅ **myseiu.be/oe-resource** ን ይጎብኙ።

Caregiver KICKS™



በየዓመቱ የእርስዎን Caregiver Kicks — ማዳለጥን የሚከለካል ጫማ — ያግኙ! ይህ ምቹ ጫማ ሲሆን በሥራ ቦታ ላይ ደኅንነትዎን ይጠብቅልዎታል ብሎም ያምራል። እንደ Reebok እና Skechers. ከመሳሰሉ ታዋቂ ስም ያላቸው ምርቶች የመጡ ከ70 በላይ ስታይሎችን ማግኘት ይችላል። የእርስዎን Caregiver Kicks እዚህ ላይ ያግኙ፡- **myseiu.be/oe-kicks**።

*Employee Assistance Program /የሥራ ተቀጣሪ ረዳት ፕሮግራም/ በ Health Advocate በኩል ከእንግዲህ ለእንክብካቤ ሰጪዎች ከኦገስት 1፣ 2021 ጀምሮ የሚገኝ አይሆንም።



Aetna IP_am-ET.indd 6 15/06/21 15:19




## የእርስዎን በሐኪም የተሰጠ መድኃኒት ማዘዣ በብልህነት ይጠቀሙበት

ሁሉንም ያልዎትን ምርጫዎች እና ምን ያክል ወጪ እንደሚጠይቁ በመረዳት በእርስዎ በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት የመድን ሽፋን ማግኘት የሚችሉትን ጥቅም በሙሉ ያግኙ።

*ዋጋ ላይ የተመረኮዙ መድኃኒቶች የተለያዩ የጤና ችግሮችን ለማከም የተዘጋጁ ጀነሪክ መድኃኒቶች ናቸው።

| **Rx** ጥምራ ክፍያ (በአውታረ መረብ ውስጥ) ለ **30** ቀናት ለሚሆን መድ ኃኒት አቅርቦት | በመድኃኒት ቤት ውስጥ | በፖስታ ቤት ትዕዛዝ |
|---|---|---|
| ጀነሪክ የወሊድ መከላከያ መድኃኒቶች | $0 | 2x መድኃኒት ማዘዣ ጣምራ ክፍያ በ 90-ቀን የመድኃኒት አቅርቦት (በአውታረ መረቡ ውስጥ ብቻ የሚገኝ) |
| ዋጋ ላይ የተመረኮዙ መድኃኒቶች* | $4 | |
| ጀነሪክ መድኃኒቶች | $8 | |
| ፎርሙላሪ ታዋቂ ስም ያላቸው መድኃኒ ቶች | $25 | |
| ፎርሙላሪ ያልሆኑ ታዋቂ ስም ያላቸው መድኃኒቶች | $50 | |

## አዲስ!

ወደ የእርስዎ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ ዶክተር (በተጨማሪ ተቀዳሚ እንክብካቤ ሰጪ በመባል ይታወቃል) የሚያደርጓቸው ጉብኝቶች በእርስዎ መድን ሽፋን አማካይነት ነጻ ናቸው።

## ድንገተኛ የሕክምና ክፍልን ከመጠቀም ውጭ ያሉ አማራጮች

| የድንገተኛ ሕክምና ክፍል | አስቸኳይ ሕክምና | ተቀዳሚ የሕክምና ምርመራ |
|---|---|---|
| **$200** ጣምራ ክፍያ | **$15** ጣምራ ክፍያ | **$0** |

አስቸኳይ የሕክምና እንክብካቤን በመጠቀም **$185** ገንዘብ ይቆጥቡ።
አፈጣኝ የሕክምና እርዳታ ማግኘት የሚያስፈልግዎት ከሆነ፣ በአቅራቢያዎ የሚገኝ የአስቸኳይ ሕክምና መስጫ ማዕከልን ያፈላልጉ ወይም ከእርስዎ ዶክተር ጋር በተመሳሳይ ቀን ቀጠሮ ይያዙ። እስከ $185 ድረስ ገንዘብ መቆጠብ ይችላሉ።

አፋጣኝ ሕክምና እንክብካቤ እንደ ድንገተኛ ሕክምና አይደለም።
እንደ ልብ ድካም ወይም ስትሮክ በመሰለ ለሞት አደጋ ሊያጋልጥ በሚችል የጤና ችግር ውስጥ ካሉ፣ ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ አለብዎት። እንደ የቁርጭምጭሚት ወለምታ የመሰለ ቀላል የሆኑ የአካል ጉዳት ወይም መቁሰል ካለብዎት ወደ አስቸኳይ ሕክምና ክፍል ይሂዱ።



Aetna IP_am-ET.indd 7 15/06/21 15:19

# የሜዲካል መድን ሽፋን ጥቅማ ጥቅም አጭር ማጠቃለያ

aetna℠

ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን:- 1/8/2021

ይህ የመድን ጥቅማ ጥቅሞች አጭር ማጠቃለያ ነው። ይህ ውል ወይም የመድን ሽፋን ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አይደለም። አማራጭ ሕክምናዎችን ጨምሮ ሁሉም የጥቅማ ጥቅም ማብራሪያዎች በሕክምና አስፈላጊ ለሆኑ አገልግሎቶች የሚሰጡ ናቸው። አባሉ የመድን ሽፋን ላለው አገልግሎት ወይም ለአገልግሎቱ በተጨባጭ የሚከፈለውን ክፍያ ያነሰ የድርሻ ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል። ገደቦችን ጨምሮ ሙሉ የመድን ሽፋን ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት፣ እባክዎ የእርስዎን የመድን ሽፋን ምስክር ወረቀት ይመልከቱ።

በ Patient Protection and Affordable Care Act of 2010 ሕግ መሠረት:-

- የመድን ሽፋን ባላቸው አስፈላጊ መሠረታዊ የጤና መድን ሽፋኖች ላይ የነበረው ከፍተኛ የዶላር እሴት ከእንግዲህ ተፈጻሚነት አይኖረውም። የሕይወት ዘመን ገደብ ላይ በመድረስ ምክንያት የመድን ሽፋናቸው ያቆመ አባላት በዚህ የመድን ሽፋን ሥር ለዚህ የመድን ሽፋን ለመመዝገብ ብቁ ናቸው።

| ጥቅማ ጥቅሞች | ተመራጭ የአገልግሎት ሰጪ አውታረ መረብ | ተመራጭ ያልሆነ የአገልግሎት ሰጪ አውታረ መረብ |
|---|---|---|
| ተቀናሽ ገንዘብ ከዕቅዱ | ዓመታዊ ያልሆነ ተቀናሽ | ነፍስ ወከፍ ተቀናሽ:- $500 በቀን መቁጠሪያ አንድ ዓመት |
| ነፍስ ወከፍ ተቀናሽ ወደ ሌላ የሚተላለፍ | ተገቢነት የለውም | 4ኛ ሩብ ዓመት ወደ ሌላ የሚተላለፍ ሒሳብ ተፈጻሚ ይሆናል |
| ጥምር ኢንሹራንስ ዕቅድ | ጥምር ኢንሹራንስ ዕቅድ የለም | የመድን ሽፋኑ ከተፈቀደው ገንዘብ መጠን 80% ሲከፍል እርስዎ ደግሞ 20% ይከፍላሉ። |
| ከኪስ የሚከፈል ገንዘብ ገደብ | ግለሰብ ከኪሱ አውጥቶ የሚከፈለው ገንዘብ ገደብ $1,200<br><br>ለሚከተሉት የመድን ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶች ከኪስ የሚ ከፈል ገንዘብ በከኪስ የሚከፈል ገንዘብ ገደብ ውስጥ የተካ ተቱ ናቸው።<br><br>የመድን ሽፋን ላላቸው ሁሉም የወጪ መጋራቶች | በአውታረ መረብ ውስጥ ካለ ጋር የተጋሩ |
| ከዚህ ቀደም የነበረ ችግር (PEC) የመጠበቂያ ጊዜ | ምንም PEC የሌለው | ልክ እንደ ተመራጭ የአገልግሎት ሰጪ አውታረ መረብ |
| የዕድሜ ልክ ከፍተኛው | ገደብ የሌለው | ልክ እንደ ተመራጭ የአገልግሎት ሰጪ ከፍተኛው |
| የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች (የሐኪም ምርመራዎች) | %15 ጣምራ ክፍያ። በ Aetna ድርጣቢያ ላይ ተቀዳሚ አገልግሎት ሰጪ ዶክተር ከመደቡ፣ በዚህ ዶክተር የሚደረጉ ሁሉም ምርመራዎች $0 ጣምራ ክፍያ ይኖራቸዋል። | $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| የሆስፒታል አገልግሎቶች | ለተኙቶ ታካሚ የሚሰጡ አገልግሎቶች:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስ ተኛት<br><br>የተመላላሽ ታካሚ ቀዶ ጥገና:- %50 ጣምራ ክፍያ | ለተኙቶ ታካሚ የሚሰጡ አገልግሎቶች:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ<br>5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት። ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ከአውታረ መረብ ውጭ ለሚሰጥ ሕክምና ፈቃድ ሳያገኙ በመቅረት ምክንያት የሚጣል የ $400 ቅጣት።<br><br>የተመላላሽ ታካሚ ቀዶ ጥገና:- $50 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች (አንዳንድ በመርፌ የሚሰጡ መድኃኒቶች በተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች ሥር የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል) | ተመራጭ ጄነሪክ መድኃኒት (ታየር 1)/ተመራጭ ታውቂ ስም ያለው(ታየር 2)/ተመራጭ ያልሆነ (ታየር 3) $4/$8/$25/$50 ጣምራ ክፍያ | ተመራጭ ጄነሪክ መድኃኒት/ተመራጭ የሆነ ታዋቂ ስም ያለው/ተመራጭ ያልሆነ<br>$13/$30/$55 ጣምራ ክፍያ |
| በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት በፖስታ ቤት የሚሰጥ ትዕዛዝ | 2 x በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት ወጪ በየ 90 ቀን አቅር ቦት የሚመደብ ድርሻ | ሽፋን የለውም |
| የደረቅ መርፌ ሕክምና (አኩፓንክቸር) | 12 ምርመራዎች በቀን መቁጠሪያ አንድ ዓመት 15% ጣምራ ክፍያ | ከተመራጭ አገልግሎት ሰጪ ጋር በየሐኪም ምርመራ ላይ የሚጋራ $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| የአምቡላንስ አገልግሎቶች | የመድን ሽፋኑ 80% ይከፍላል እርስዎ 20% ይከፍላሉ | ልክ እንደ ተመራጭ የአገልግሎት ሰጪ የመድን ሽፍን ጥቅማ ጥቅም |

### የ **Aetna Health Plan** የመድን ሽፋን ጥቅማ ጥቅም አጭር ማጠቃለያ፣ ካለፈው የቀጠለ።

| ጥቅማ ጥቅሞች | ተመራጭ የአገልግሎት ሰጪ አውታረ መረብ | ተመራጭ ያልሆነ የአገልግሎት ሰጪ አውታረ መረብ |
|---|---|---|
| የኬሚካል ጥገኝነት | ተኝቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት 5 ቀን<br>ተመላላሽ ታካሚ:- %0 ጣምራ ክፍያ | ተኝቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት እና የጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል ከአውታረ መረብ ውጭ ለሚሰጥ ሕክምና ፈቃድ ሳያገኙ በመቅረት ምክንያት የሚጣል የ $400 ቅጣት።<br>ተመላላሽ ታካሚ:- $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| መሣሪያዎች፣ ማሽኖች እና አቅርቦቶች<br>• ረዥም ጊዜ የሚቆይ ሜዲካል መሣሪያ<br>• ኦርቶፔዲክ (የአጥንት) ኢጋዥ ሕክምና መገልገያዎች<br>• ድኅረ ማስቴክቶሚ ብራዎች (የሕክምና ጡት ማስያዣዎች)<br>• በሁለት (2) የተገደበ በየ<br>• ስድስት (6) ወሩ የሚሰጥ<br>• የኦስቶሚ አቅርቦቶች<br>• ፕሮስቴቲክ መሣሪያዎች | በ50% መድን ሽፋን ያላቸው | በ50% መድን ሽፋን ያላቸው፣ ተቀናሾች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል |
| የስኳር በሽታ አቅርቦቶች | ኢንሱሊን፣ መርፌዎች፣ ሲሪንጆች እና ላንሴትሲ በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች። ከውጭ የሚሰጥ ኢንሱሊን መግፊያ (ፓምፖች)፣ የደም ግሉኮስ መቆጣጠሪያዎች፣ የምርመራ ሪኤጀንቶች እና አቅርቦቶች - መሣሪያዎች፣ ማሽኖች እና አቅርቦቶች የሚለውን ይመልከቱ። መሣሪያዎች፣ ማሽኖች እና አቅርቦቶች ወይም በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች የመድን ሽፋን ሲኖራቸው እና የመድን ሽፋን ገደቦች ሲኖርባቸው የስኳር በሽታ አቅርቦቶች እነዚህ ገደቦች አይመለከታቸውም። | ኢንሱሊን፣ መርፌዎች፣ ሲሪንጆች እና ላንሴትሲ በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች። ከውጭ የሚሰጥ ኢንሱሊን መግፊያ (ፓምፖች)፣ የደም ግሉኮስ መቆጣጠሪያዎች፣ የምርመራ ሪኤጀንቶች እና አቅርቦቶች - መሣሪያዎች፣ ማሽኖች እና አቅርቦቶች የሚለውን ይመልከቱ። መሣሪያዎች፣ ማሽኖች እና አቅርቦቶች ወይም በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች የመድን ሽፋን ሲኖራቸው እና የመድን ሽፋን ገደቦች ሲኖርባቸው የስኳር በሽታ አቅርቦቶች እነዚህ ገደቦች አይመለከታቸውም። |
| የምርመራ ላብራቶሪ ኣና የራጂ አገልግሎቶች | ተኝቶ ታካሚ:- በሆስፒታል አገልግሎቶች ሥር የመድን ሽፋን ያለው<br>ተመላላሽ ታካሚ:- ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው | ተኝቶ ታካሚ:- በሆስፒታል አገልግሎቶች ሥር የመድን ሽፋን ያለው<br>ተመላላሽ ታካሚ:- ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ተፈጻሚ ይሆናሉ። |
| የድንገተኛ አደጋ አገልግሎቶች (ተኝቶ እንዲተከም ከተደረገ ጣምራ ክፍያ በይለፈኝ ይታለፋል) | %200 ጣምራ ክፍያ | %200 ጣምራ ክፍያ |
| የጆሮ ምርመራዎች (መደበኛ) | %15 ጣምራ ክፍያ | $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| ኢጋዥ ማዳመጫ መሣሪያ | በተለየ የመድን ዕቅድ የሚሸፈን:- EPIC ማዳመጫ። ጣምራ ክፍያ የለም፣ እስከ $1,200 በየእያንዳንዱ ጆሮ በየ 3 ዓመታት ኢጋዥ ማዳመጫውን ወጪ ለመሸፈን። የበለጠ በ myseiu.be/hearing ላይ ይረዱ | በተለየ የመድን ዕቅድ የሚሸፈን:- EPIC ማዳመጫ። ጣምራ ክፍያ የለም፣ እስከ $1,200 በየእያንዳንዱ ጆሮ በየ 3 ዓመታት ኢጋዥ ማዳመጫውን ወጪ ለመሸፈን። የበለጠ በ myseiu.be/hearing ላይ ይረዱ |
| የቤት ውስጥ የጤና አገልግሎቶች | በአንድ የቀን መቁጠሪያ ዓመት እስከ 130 የሐኪም ምርመራዎች የመድን ሽፋን ያለው | ከተመራጭ አገልግሎት ሰጪ ጋር በየሐኪም ምርመራ ላይ የሚጋራ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ከአውታረ መረብ ውጭ ለሚሰጥ ሕክምና ፈቃድ ሳያገኙ በመቅረት ምክንያት የሚጣል የ $400 ቅጣት። |
| የሆስፒስ አገልግሎቶች | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው | ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ከአውታረ መረብ ውጭ ለሚሰጥ ሕክምና ፈቃድ ሳያገኙ በመቅረት ምክንያት የሚጣል የ $400 ቅጣት። |
| የመካንነት ሕክምና አገልግሎቶች | አርቴፊሻል የወንድ ዘር ማመንጨት፣ ኢን-ቪትሮ እንቁላል ማቋት እና የመድኃኒት ሕክምና ጨምሮ ለወንድ እና ለሴት መካንነት ሕክምና የሚሰጡ ሜዲካል እና የቀዶ ጥገና አገልግሎቶች እና ሁሉም ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶች ተገቢነት ያላቸው የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች የወጪ መጋራቶች እንደተጠበቁ ሆነው እስከ $5,000 በዕድሜ ልክ ከፍተኛ ድረስ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል።<br>የመካንነት መድኃኒቶች ተቀናሾች እና 20% የመድን ሽፋን ጣምራ ኢንሹራንስ ዕቅድ መሠረት የመድን ሽፋን አላቸው፣ እስከ $5,000 በዕድሜ ልክ ከፍተኛ ድረስ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል። | ሽፋን የለውም |
| ማኑፒሌቲቭ ቴራፒ | ያለ ምንም ቅድሚያ ፈቃድ በአንድ የቀን መቁጠሪያ ዓመት እስከ 12 ምርመራዎች<br>የመድን ሽፋን ያለው<br>%15 ጣምራ ክፍያ | በአውታረ መረብ ውስጥ ካለ ጋር ለተጋሩ የተገደቡ ምርመራዎች<br>$15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| የማሳጅ አገልግሎቶች | $15 ጣምራ ክፍያ (12 ምርመራዎች በቀን መቍጠሪያ አንድ ዓመት) | ከተመራጭ አገልግሎት ሰጪ ጋር በየሐኪም ምርመራ ላይ የሚጋራ<br>$15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| የእመጫትነት አገልግሎቶች | ተኝቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት 5 ቀን<br>ተመላላሽ ታካሚ:- %15 ጣምራ ክፍያ። መደበኛ ሕክምና የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች ጣምራ ክፍያ አይመለከተውም። | ተኝቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት እና የጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል። ከአውታረ መረብ ውጭ ለሚሰጥ ሕክምና ፈቃድ ሳያገኙ በመቅረት ምክንያት የሚጣል የ $400 ቅጣት።<br>ተመላላሽ ታካሚ:- $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል። መደበኛ ሕክምና የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች ጣምራ ክፍያ አይመለከተውም። |



Aetna IP_am-ET.indd 9 15/06/21 15:19

| ጥቅማ ጥቅሞች | ተመራጭ የአገልግሎት ሰጪ አውታረ መረብ | ተመራጭ ያልሆነ የአገልግሎት ሰጪ አውታረ መረብ |
|---|---|---|
| የአእምሮ ጤና | ተኙቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ<br>በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት 5 ቀን<br>ተመላላሽ ታካሚ:- %0 ጣምራ ክፍያ | ተኙቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእ ያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት እና የጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል<br>ከአውታረ መረብ ውጭ ለሚሰጥ ሕክምና ፈቃድ ሳያገኙ በመቅረት ምክንያት የሚጣል የ $400 ቅጣት።<br>ተመላላሽ ታካሚ:- $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| ናቹሮፓዚ | $15 ጣምራ ክፍያ (12 ምርመራዎች በቀን መቁጠሪያ አንድ ዓመት) | ከተመራጭ አገልግሎት ሰጪ ጋር በየሐኪም ምርመራ ላይ የሚጋራ $15 ገደብ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ተፈጻሚ ይሆናሉ። |
| የአራስ ሕፃን አገልግሎቶች | የመጀመሪያ የሆስፒታል ቆይታ:- የሆስፒታል አገልግሎቶችን ይመልከቱ፣ የሐኪም ምርምራዎች:- የተመላላሽ ታካሚ አገልግ ሎቶችን ይመልከቱ፤ መደበኛ የጤና ምርመራ አገልግሎት:- መከ ላከያ እንክብካቤን ይመልከቱ። ለአራስ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግ ሎቶች ላይ ተፈጻሚነት ያለው ማናቸውም የወጪ መጋራት ከእና ትየው የተለየ ነው> | የመጀመሪያ የሆስፒታል ቆይታ:- የሆስፒታል አገልግሎቶችን ይመልከቱ፣ የሐኪም ምርምራዎች:- የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶችን ይመልከቱ፤ መደበኛ የጤና ምርመራ አገልግሎት:- መከላከያ እንክብካቤን ይመል ከቱ። ለአራስ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚነት ያለው ማናቸውም የወጪ መጋራት ከእናትየው የተለየ ነው> |
| ከቅጥ ያጣ ውፍረት ጋር የተገናኘ ቀዶ ጥገና (ባሪያትሪክ) | የሕክምና መስፈርት ሲሟላ በወጪ መጋራት ወቅት ሽፋን ይኖ ረዋል | ሽፋን የለውም |
| የውስጥ ብልት ትክለ ነቀላዎች | ገደብ የሌለው፣ ምንም መጠበቂያ ጊዜ የለውም<br>ተኙቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት<br>ተመላላሽ ታካሚ:- %15 ጣምራ ክፍያ | ሽፋን የለውም |
| የመከለከያ እንክብካቤ<br>(የጤናማነት እንክብካቤ አካላዊ፣ ክትባት፣ ፓፕ ስሚር ምርመራዎች፣ ማሞግ ራሞች) | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው<br><br>የሴቶች መከለከያ እንብካቤ አገልግሎቶች (የወሊድ መከላከያ ዘዴ መድኃኒቶች ኣና መሣሪያዎች እንዲሁም መሃን ማድረግ ጨምሮ) ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን አላቸው። | ሽፋን የለውም<br><br>የሴቶች መከለከያ እንብካቤ አገልግሎቶች (የወሊድ መከላከያ ዘዴ መድ ኃኒቶች ኣና መሣሪያዎች እንዲሁም መሃን ማድረግ ጨምሮ) ተገቢነት ባለው የመከለከያ እንክብካቤ የወጪ መጋራት እና የጥቅማ ጥቅም ከፍ ተኛዎች ተገዢ ነው።<br><br>መደበኛ ማሞግራሞች ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ተፈጻሚ ይሆናሉ። |
| የመልሶ መቋቋሚያ አገልግሎቶች<br>(የመልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች በቀን መቁ ጠሪያ አንድ ዓመት ውስጥ ያሉት ምርመራ ዎች ድምር ጥምረት ነው) | ተኙቶ ታካሚ:- 60 ቀናት በቀን መቁጠሪያ አንድ ዓመት። ከአ እምሮ ጤና ምርመራ ጋር የተገናኙ አገልግሎቶች ያለ ምንም ገደብ የመድን ሽፋን አላቸው። $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት<br>ተመላላሽ ታካሚ:- 60 ምርመራዎች በቀን መቁጠሪያ አንድ ዓመት። ከአእምሮ ጤና ምርመራ ጋር የተገናኙ አገልግሎቶች ያለ ምንም ገደብ የመድን ሽፋን አላቸው። %15 ጣምራ ክፍያ | ተኙቶ ታካሚ:- ከተመራጭ አገልግሎት ሰጪ የመድን ሽፋን ጋር የሚጋራ የሕክምና ምርመራ የቀን ገደቦች $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት። ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ተፈጻሚ ይሆናሉ።<br>ተመላላሽ ታካሚ:- ከተመራጭ አገልግሎት ሰጪ የመድን ሽፋን ጋር የሚጋራ የሕክምና ምርመራ ገደቦች $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| የሠለጠነ የነርስ አገልግሎት ተቋም | በአንድ የቀን መቁጠሪያ ዓመት እስከ 60 ቀናት የመድን ሽፋን ያለው | ከተመራጭ አገልግሎት ሰጪ የመድን ሽፋን ጋር የሚጋራ የቀን ገደብ፣ ተቀናሽ እና የጣምራ ኢንሹራን ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ከአውታረ መረብ ውጭ ለሚሰጥ ሕክምና ፈቃድ ሳያገኙ በመቅረት ምክንያት የሚጣል የ $400 ቅጣት። |
| መሀን ማድረግ<br>(ቫስክቶሚ፣ ቲዩባል ሊጌሽን) | ተኙቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት<br><br>ተመላላሽ ታካሚ:- %15 ጣምራ ክፍያ<br><br>የሴቶች መሀን ማድረግ ሕክምና ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን አላቸው። | ተኙቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእ ያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት እና የጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል<br>ተመላላሽ ታካሚ:- $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል<br><br>የሴቶች መሃን የማድረግ ሕክምናዎች ተገቢነት ባለው የመከላከያ ሕክምና እንክብካቤ የመድን ወጪ ሽፋን ድርሻ እና የመድን ጥቅማ ጥቅም ከፍተኛዎች ላይ በመመርኮዝ የመድን ሽፋን ያገኛሉ። |
| Temporomandibular Joint (TMJ) አገልግሎቶች | ተኙቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት<br><br>ተመላላሽ ታካሚ:- %15 ጣምራ ክፍያ | ተኙቶ ታካሚ:- $100 ጣምራ ክፍያ፣ በቀን እስከ 5 ቀናት ድረስ በእ ያንዳንዱ ሆስፒታል ማስተኛት እና የጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል<br><br>ተመላላሽ ታካሚ:- $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራ ንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| የሲጋራ ማቆም ምክር አገልግሎት | ከዕድሜ ልክ ፕሮግራም አቋርጦ መውጣት - ሙሉ በሙሉ መድን ሽፋን ያለው | ተገቢነት ያላቸው ወጪ መጋራቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ |
| መደበኛ የምርመራ አገልግሎት<br>(1 ምርመራ በየ 12 ወሩ) | %15 ጣምራ ክፍያ | $15 ጣምራ ክፍያ፣ ተቀናሽ እና ጣምራ ኢንሹራንስ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል |
| ኦፕቲካል (የዓይን) መገልገያዎች<br>(መነጽር መስታወቶች፣ ኮንታክት ሌንሶችን እና ፍሬሞችን ጨምሮ) | ዕድሜያቸው ከ19 በታች የሆኑ አንድ የመንጽር ፍሬም እና መስ ታውት በዓመት ወይም በ50% ጣምራ ኢንሹራንስ መድን ሽፋን ያላቸው ኮንታክት ሌንሶች<br>የአባል ዕድሜ 19 እና ከዚያ በላይ $300 በየ 12 ወራት | ከተመራጭ አገልግሎት ሰጪ የመድን ሽፋን ጋር የሚጋራ |



Aetna IP_am-ET.indd 10 15/06/21 15:19

# የእርስዎ የጥርስ ሕክምና የመድን ዕቅዶች ምርጫ

| አገልግሎት ሰጪዎች | ዓመታዊ ከፍተኛ | ተቀናሽ | ለተለመዱ ምርመራዎ የጣምራ ክፍያ | ልዩ ባሕሪያት |
|---|---|---|---|---|
| DELTA DENTAL® | $2,000 | $0 | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው | • ገጠራማ አካባቢዎችን ጨምሮ መጠነ ሰፊ የአገልግሎት ሰጪዎች አውታረ መረብ |
| Willamette Dental Group | ምንም | $0 | ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን ያለው | • በ 1-5 ኮሪደር ውስጥ የሚኖሩ ምቹ የሆኑ እንክብካቤ ሰጪዎች<br>• ከፍተኛ የጥርስ ሕክምና ወጪዎች ላሉባቸው እንክብካቤ ሰጪዎች ምንም ዓመታዊ ከፍተኛ አይኖርም። |

## የእርስዎ የጥርስ ሕክምና የመድን ዕቅድ በእርስዎ ወርኃዊው ጣምራ አርቦን (ፕሪሚየም) **$25** ላይ የተጠቃለለ ነው።

**ሁለቱም የጥርስ ሕክምና መድን አቅዶች የኦርቶዶንቲያ ጥቅማ ጥቅሞችን ያቀርባሉ።**

የእርስዎን የጥርስ ሕክምና የመድን ዕቅድ መቀየር ይፈልጋሉ? ከጁላይ 20፣ 2021 በፊት የጤና መድን ጥቅማ ጥቅሞች ማመልከቻውን ይሙሉት እና መልሰው ያስገቡት።

---

DELTA DENTAL®

## ፒፒኦ ዕቅድ

ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን **8/1/2021**

ጥቅማ ጥቅም የሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ:- 1/1/2022 - 31/12/2022
የጥቅማ ጥቅም የሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ* (በግለሰብ፤ በክላስ **1** ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም):- $2,000
ኦርቶዶንቲያ - ዓዋቂ ሰዎች እና ሕፃናት:- 50%
የዕድሜ ልክ ከፍተኛው (በግለሰብ):- $2,000

| | Delta Dental PPO Dentist | Delta Dental Premier Dentist | ተሳታፊ ያልሆነ የጥርስ ሐኪም |
|---|---|---|---|
| **ጥቅማ ጥቅም የሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ ተቀናሽ** | | | |
| በአውታረ መረብ ውስጥ ላለ ክላስ 1 ተፈጻሚ አይሆንም - በአውታረ መረብ ውስጥ ተቀናሽ የለም - $50 በእያንዳንዱ የጥቅማ ጥቅም የሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ | $0/$50 | $50 | $50 |
| **ክላስ 1 - የሕክምና ምርመራ እና መከላከያዎች** | | | |
| ምርመራዎች<br>ጽዳት ሥራ<br>ፍሎራይድ<br>ራጂዎች<br>ሲላንቶች | 100% | 80% | 80% |
| **ክላስ 2 - ጥገና ሥራ** | | | |
| ጥገና ሥራዎች<br>ፖስተሪየር ኮምፖዚይት ሙሌቶች<br>ኢንዶዶንቲክስ (የጥርስ ሥር)<br>ፔሪዮዶንቲክስ<br>የአፍ ቀዶ ጥገና ሕክምና | 100% | 60% | 60% |
| **ክላስ 3 - ከፍተኛ ሕክምና** | | | |
| ዴንቸሮች<br>ከፊል ዴቸሮች<br>ኢምፕላንትስ<br>ብሪጆች<br>ክራውንስ | 80% | 40% | 40% |

* በዚህ ዓመት አዲስ! የእርስዎ ዓመታዊ ከፍተኛ የእርስዎ ኢንሹራንስ በአንድ ዓመት ሽፋን የሚሰጠው ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ነው። በዚህ የገንዘብ መጠን ልክ ለሚሠራ የጥርስ ሕክምና ሥራ፣ ከክላስ 1 ወጪዎች በስተቀር ከኪስዎት ወጪ አድርገው መክፈል ይኖርብዎታል።

እባክዎ ልብ ይበሉ:- ይህ ለንጽጽር ዓላማዎች ብቻ የቀረቡ የጥቅማ ጥቅሞች አጭር ማጠቃለያ ነው እና እንደ አገልግሎት ውል ሆኖ ሊቆጠር አይችልም። በአንድ የመድን ዕቅድ ውስጥ አንድ ጊዜ ከተመዘገቡ በኋላ፣ የእርስዎን Delta Dental PPO መድን ዕቅድ ይበልጥ ዝርዝሮችን የሚሰጠውን የእርስዎን የጥቅማ ጥቅሞች አነስተኛ መጽሐፍ ማግኘት ይችላሉ። ማናቸውም ጥያቄ ካልዎት ወደ የእኛ የደንበኛ አገልግሎት ክፍል ለመደወል እባክዎ ነጻ ይሁኑ ወይም የእኛን የድር ጣቢያ DeltaDentalWA.com ይጎብኙ።

# ከእርስዎ ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘት የሚችሉትን ሁሉ ያግኙ!

### የ **MySmile®** መለያ ይፍጠሩ

ወደ የእርስዎ መታወቂያ ካርድ፣ የጥቅማ ጥቅሞች መረጃ፣ ከኪስ ወጪ ተደርጎ የሚከፈል ገንዘብ ግምቶች እና ተጨማሪ ነገሮችን ለደኅንነት አስተማማኝ የሆነ፣ በቀን 24 ሰዓት/በሳምንት 7 ቀን መዳረሻ ይሰጥዎታል! የእኛ “Find your member ID” መሣሪያ ምዝገባ ማከናወንን ቀላል ያደርገዋል። የእርስዎን መለያ ለመፍጠር DeltaDentalWA.com ን ይጎብኙ።

### በአውታረ መረብ ውስጥ ያለ የጥርስ ሐኪም ይምረጡ

የእርስዎ የመድን ዕቅድ ወደ Delta Dental PPO አውታረ መረብ መዳረሻ ይሰጡዎታል። ሆኖም ግን፣ የሚገኙት ጥቅማ ጥቅሞች Delta Dental PPO የጥርስ ሐኪምን በሚጎበኙበት ጊዜ ከዚህም በላይ ብዙ ርቀት ይሄዳሉ። በእርስዎ አውታረ መረብ ውስጥ ያለ የጥርስ ሐኪምን ለማግኘት DeltaDentalWA.com ን ይጎብኙ (እንዴት እንደሚቻል በሚቀጥለው ገጽ ላይ ይረዱ)።

የእርስዎ የመድን ዕቅድ አስፈላጊ ከሆነ ከእርስዎ አካባቢ ውጭ ያለ የ PPO ጥርስ ሐኪምን ማግኘት እንዲችሉ መዳረሻ ከሚሰጥዎት Delta Dental Premier® አውታረ መረብ ጋር አብሮ ይመጣል። ይህ ማለት ከአውታረ መረብ ውጭ ያሉ ከፍተኛ ወጪዎችን ከመክፈል ይቆጠባሉ ማለት ነው (ከዚህ በታች ያለውን ቻርት ይመልከቱ)።

### ተጨማሪ የጥርስ ሕክምና ሥራዎች የመድን ሽፋን አላቸው

የክላስ 1 ወጪዎች በእርስዎ ዓመታዊ ከፍተኛ ላይ አይቆጠሩም፣ ይህም ማለት አብዛኛው የእርስዎ የክላስ 2 እና 3 ወጪዎች በመድን ኢንሹራንሱ የሚሸፈኑ ይሆናሉ ማለት ነው።

| | PPO | ፕሪሚየር | ከአውታረ መረብ ውጭ |
|---|---|---|---|
| የእርስዎ የመድን ዕቅድ የጥርስ ሕክምና አውታረ መረብ | ✓ | | |
| ጥቅማ ጥቅሞች ብዙ ርቀት ይሄዳሉ ይህም ማለት ከኪስ ወጪ የሚከፈለው ገንዘብ አነስተኛ ይሆናል | ✓ | | |
| የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅጾች ፋይሎች ለእርስዎ | ✓ | ✓ | |
| ከእኛ የጥራት አስተዳደር እና የወጪ ጥበቃ ጋር አብሮ ይመጣል | ✓ | ✓ | |
| ምንም የወጪ ጥበቃ የለም ማለት ከኪስ ወጪ የሚከፈለው ገንዘብ ከፍተኛ ይሆናል | | | ✓ |

### በእርስዎ አቅራቢያ በአውታረ መረብ ውስጥ ያለ የጥርስ ሐኪምን ያግኙ

1. ይህን ይጎብኙ **DeltaDentalWA.com**
2. በ ኦንላይ መገልገያዎች (Online Tools) ላይ ጠቅ ያድርጉ እና የእኛን ‘የጥርስ ሃኪም አግኝ (Find a Dentist)’ መሣሪያ ይጠቀሙ
3. የእርስዎን የፍለጋ ውጤቶች ለማጣራት ‘Delta Dental PPO’ ይምረጡ

### በእርስዎ የጥርስ ሐኪም በመደበኛነት ይታዩ።

የእርስዎ መድን ዕቅድ በየዓመቱ የሚደረጉ የመከላከያ እንክብካቤዎችን ይሸፍናል። በየቀኑ ጥርስን ማጽዳት እና በመደበኛነት በሐኪም መታየት የአርስዎን ፈገግታ ጤናማ ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ እና ስቃይ የተሞላ ውድ ችግሮችን ከመምጣታቸው በፊት ለመከላከል አስፈላጊ ናቸው።

### ከኪስ ወጪ ሆኖ የሚከፈል ክፍያ መጠን ግምቶች።

የእርስዎን ወጪ ማወቅ መቻል እርስዎን እና የእርስዎን የጥርስ ሐኪም የእርስዎን ጥቅማ ጥቅሞች ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ ሕክምናውን ዕቅድ እንዲታወጡለት ያግዛችኋል።

**MySmile Cost Genie℠** ቅጽበታዊ የወጪ መጠን ግምቶችን ይሰጥዎታል። እንደ ሙሌቶች ለመሳሰሉ መሠረታዊ ሕክምናዎች በጣም ጥሩ ነው። ለእርስዎ በግል የተዘጋጁ ግምቶችን ለማግኘት ወደ የእርስዎ MySmile መለያ በቀላሉ ይግቡ።

እንደ ክራውን የመሳሰለ የተራዘመ ሕክምና በሚፈልጉበት ጊዜ የእርስዎን የጥርስ ሐኪም “ቅድሚያ ግምት ማረጋገጫ” እንዲሰጥዎት ይጠይቁ። ከእርስዎ የጥርስ ሐኪም የሕክምና እና ወጪ ማረጋገጫ ያገኛሉ። ይህ የአርስዎን የሕክምና ዕቅድ፣ የእርስዎ የመድን ዕቅድ ምንን እንደሚሸፍን እና ለእርስዎ የጥርስ ሐኪም ምን ያክል መክፈል እንዳለብዎት ዝርዝር ይሰጣል።



## ጥያቄዎች አልዎት?
## ወደ **Delta Dental** ይደውሉ።
## **1-800-554-1907**

ከሰኞ እስከ ዓርብ፦ 7 a.m. እስከ 5 p.m. በፓስፊክ ሰዓት አቆጣጠር



Aetna IP_am-ET.indd 12 15/06/21 15:19

Willamette
Dental Group

# የጥርስ ሕክምና ዕቅድ

*ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን* **8/1/2021**

በ Willamette Dental of Washington, Inc የተጻፈ። ይህ የመድን ዕቅድ የጥርስን እና ድጋፊ ሥጋዎችን በሽታዎች ወይም የጤና ችግሮች ለመከላከል፣ ለመመርመር ወይም ለማከም የሚያስችሉ የተራቀቁ የአገልግሎቶችን ሽፋን ያቀርባል። እዚህ ላይ የቀረቡት አብዛኛዎቹ በብዛት በእርስዎ የመድን ሽፋን ዕቅድ ላይ ካሉ አሠራሮች መካከል አንዳንዶች ናቸው። ሙሉ የመድን ሽፋን ዕቅድ ዝርዝር ማብራሪያን፣ ገደቦችን እና ተለይተው የሚቀሩ ነገሮችን ለማግኘት የመድን ሽፋን ምስክር ወረቀቱን እባክዎ ይመልከቱ።

| ጥቅማ ጥቅሞች | ጣምራ ክፍያዎች |
|---|---|
| ዓመታዊ ከፍተኛ | ምንም ዓመታዊ ከፍተኛ የለም* |
| ተቀናሽ | ምንም ተቀናሽ የለም |
| አጠቃላይ እና የኦርቶዶንቲክ የሐኪም ምርመራዎች | ምንም የጣምራ ክፍያ በእያንዳንዱ ምርመራ አይኖርም |
| **ምርመራ እና መከላከያ አገልግሎቶች** | |
| መደበኛ እና ድንገተኛ ምርመራዎች፣ ራጂዎች፣ የጥርስ ማጽዳት፣ የፍሎራ ይድ ሕክምና፣ ሲያላንቶች (በእያንዳንዱ ጥርስ)፣ የጭንቅላት እና የአንገት ካንሰር ምርመራ፣ የአፍ ንጽሕና መመሪያ፣ ፔሪዶንታል ቻርቲንግ፣ ፔሪዶንታል ምርመራ | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| **የጥገና የጥርስ ሕክምና ሥራ** | |
| ሙሌቶች (አማልጋም) | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| ፕሮክሌን-ሜታል ክራውን | እርስዎ $250 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **ፕሮስቶንዶንቲክስ** | |
| የላይኛው ወይም የታችኛው ሙሉ ዴንቸር | እርስዎ $400 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| ብሪጅ (በጥርስ) | እርስዎ $250 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **ኤንዶቶንቲክስ እና ፔሪዮዶንቲክስ** | |
| የሩት ካናል ቴራፒ - አንተሪዮር | እርስዎ $85 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| የሩት ካናል ቴራፒ - ባይኩስፒድ | እርስዎ $105 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| የሩት ካናል ቴራፒ - ሞላር | እርስዎ $130 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| ኦሲዮስ ቀዶ ጥገና (በእያንዳንዱ ኳድራንት) | እርስዎ $150 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| ሩት ፕላኒንግ (በእያንዳንዱ ኳድራንት) | እርስዎ $75 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **የአፍ ቀዶ ጥገና ሕክምና** | |
| መደበኛ ጥርስ ነቀላ (አንድ ጥርስ) | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| በቀዶ ጥገና ጥርስ ነቀላ | እርስዎ $100 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **የኦርቶዶንቲያ ጥርስ ሕክምና** | |
| ቅድመ የኦርቶዶንቲያ ጥርስ ሕክምና | እርስዎ $150 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| ሁሉን አቀፍ የኦርቶዶንቲያ ጥርስ ሕክምና | እርስዎ $2,500 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| **ጥርስ ገጠማ** | |
| የጥርስ ገጠማ ቀዶ ጥገና | የጥርስ ገጠማ ጥቅማ ጥቅም ከፍተኛ $1,500 በቀን መቁጠሪያ አንድ ዓመት |
| **የተለያዩ ጉዳዮች** | |
| በቦታው ላይ የሚሰጥ ማደንዘዣ | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| የጥርስ ላብራቶሪ ክፍያዎች | በሐኪም ምርመራ ጣምራ ክፍያ በኩል የመድን ሽፋን ያለው |
| ኒትሩስ ኦክሳይድ | እርስዎ $40 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| የስፔሻል ዶክተር ሕክምና ምርመራ | በእያንዳንዱ ምርመራ እርስዎ $30 ጣምራ ክፍያ ይከፈላሉ |
| ከአካባቢ ውጭ የተሰጠ ድንገተኛ ሕክምና ወጪን መልሶ መክፈል | ከ$250 በላይ ለሆነ ለሚመጡ ክፍያዎች እርስዎ ይከፍላሉ |

*TMJ ዓመታዊ ከፍተኛ $1000 / $5000 የዕድሜ ልክ ከፍተኛ አለው
**ታካሚው የሕክምና ዕቅዱን ተስማምቶ ከተቀበለ ጣምራ ገቢ በሁሉን አቀፍ ኦርቶዶንቲያ ሕክምና ጣምራ ክፍያ ላይ ገቢ ይደረጋል።



Aetna IP_am-ET.indd 13 15/06/21 15:19

## ተለይተው የሚቀሩ

ፕሮስቴቲክ ዕቃው ከተገጠመ በኋላ የመድን ሽፋኑ ካበቃ ከ60 ቀናት በላይ ከሆነው በርካታ የሕክምና ቀጠሮ ቀናትን ወይም ማስተካከያዎችን የሚጠይቁ ብሪጆች፣ ክራውኖች፣ ዴንቸሮች ወይም ፕሮስቴቲክ መሣሪያዎች።

ዓባሪ መሣሪያዎችን፣ ጥገና እና የጥርስ ተከላ ተዛማጅ አገልግሎቶችን ጨምሮ የጥርስ ተከላዎች የመድን ሽፋን ተፈጻሚ ከሚሆንበት ቀን ቀደም ብለው የተጀመሩ ሕክምናዎችን ወይም አገልግሎቶችን ማጠናቀቂያ ወይም መስጫ።

ከመድን ሽፋኑ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን ቀደም ብለው የተሰጡ ኢንዶዶንቲክ አገልግሎቶች፣ ፕሮስቴቲክ አገልግሎቶች እና ጥርስ ተከላዎች። ከመድን ሽፋኑ ማብቂያ ቀን በኋላ ከ60 ቀናት በላይ ቆይቶ የተጠናቀቀ ኢንዶዶንቲክ ቴራፒ። የመድን ሽፋን ከሌለው አገልግሎት ጋር በተገናኘ በተለይ የሚደረጉ የሕክምና ምርመራዎች ወይም ምክክሮች። የሙከራ ወይም የምርምር አገልግሎቶች እና ተዛማጅ ምርመራዎች ወይም ምክክሮች።

ከክራውኖች፣ ብሪጆች ወይም የጥርስ ተከላዎች ጋር የሚደረግ የተራቀቀ ማስተካከያን ጨምሮ ወይም ማሸግን፣ ተቆልቋይ ዳይሜንሽንን መቀየር፣ አክሉሽንስን ወደ ነበሩበት መመለስ ወይም መጣመምን፣ መጋጥን ወይም መሸርሸርን ማስተካከል ጨምሮ ሙሉ የአፍ እንደገና ማስተካከያ።

ለጥርስ የሕክምና ዘዴዎች፣ የሐኪም አገልግሎቶች ወይም ለተቋም ክፍያዎች ከጥርስ ሕክምና ማዕከሉ ውጪ በሆስፒታል በመተኛት የሚሰጥ ሕክምና። ማክሲሎፋሺያል ፕሮስቴቲክ አገልግሎቶች።

የሌሊት ጥርስ ምላስን እንዳይነክስ ማገጃ።

የግል ልዩ ማስተካከያ ሕክምናዎች።

በተለይ መልክን ለማሻሻል፣ ለመለወጥ ወይም ለማላቅ በዋንኛነት የታሰቡ የፕላስቲክ፣ ዳግም ማስተካከያ ወይም ኮስሞቴክ ቀዶ ጥገና እና ሌሎች አገልግሎቶች ወይም አቅርቦቶች።

የመድኃኒት ማዘዣ እና ያለ ሐኪም ትዕዛዝ የሚሸጡ መድኃኒቶች እና ቅድመ ሕክምና አገልግሎቶች።

ከ24 ሰዓት በቅድሚያ ከሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ውጭ ላመለጡ ቀጠሮዎች ወይም ለተሰረዙ ቀጠሮዎች አገልግሎት ሰጪው ክፍያ ሲያስከፍል።

የጠፉ፣ የታጡ ወይም የተሰረቁ ጥርስ ላይ የሚገጠሙ ነገሮች፤ በአግባቡ ካለመጠቀም፣ በአያያዝ ጉድለት ወይም ቸልተኝነት ለተበላሹ ጥርስ ላይ የሚገጠሙ ነገሮች መተኪያ።

የድምፅ ወደነበረበት ለመመለስ የሚደረግ ማስተካከያ።

በሐኪም በታዘዘው የሕክምና ዕቅድ እና/ወይም በ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም ያልተመከሩ እና ያልተፈቀዱ አገልግሎቶች እና ተዛማጅ ምርመራዎች ወይም ምክክሮች።

ካለው ተጨባጭ የጤና ችግር ምርመራ፣ እንክብካቤ ወይም ሕክምና ዓይን ሲታዩ አስፈላጊ የማይባሉ አገልግሎቶች እና ተዛማጅ ምርመራዎች ወይም ምክክሮች።

ፈቃድ ካለው የጥርስ ሐኪም፣ ዴንቱሪስት፣ ሃይጂኒስት ወይም የጥርስ ሕክምና ረዳት ውጭ ባለ በማናቸውም ሰው የሚሰጡ አገልግሎቶች።

በፕሮፌሽናል የአትሌቲክስ ውድድር ላይ በመሳተፍ ወይም በመወዳደር ወቅት ለደረሰ ጉዳት የሚሰጥ ሕክምና አገልግሎቶች።

በሠራተኛ በሥራ ቦታ ላይ የሚደርስ ጉዳት ካሣ ሥር የመድን ሽፋን ያላቸው ወይም የቀጣሪው ኃላፊነት የሆኑ አካል ጉዳቶች ወይም በሽታዎች ሕክምና አገልግሎቶች።

ሆን ተብሎ በገዛ ራስ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች ሕክምና የሚሰጡ አገልግሎቶች።

ሕግ የሚያስገድድ ካልሆነ በቀር የአገልግሎቱ የመድን ሽፋኑ በማናቸውም የፌደራል፣ የስቴት ወይም ሌላ የመንግሥት ፕሮግራም ሥር ሊገኝ የሚችል ሲሆን።

በውሉ ላይ ሽፋን እንዳላቸው ተደርገው ያልተዘረዘሩ አገልግሎቶች።

የመድን ሽፋን ካላቸው የመከላከያ አገልግሎቶች ውጪ የፓቶሎጂ፣ የዳይስፋንክሽን፣ ወይም በሽታ ማስረጃ የሌለው አገልግሎት ሲሆን።

## ገደቦች

አማራጭ አገልግሎቶች አንድን የጤና ችግር ለማከም ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ፣ በ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም የሚመከር አገልግሎት የመድን ሽፋን ይኖረዋል።

የጥርስን ተግባር የሚያሰናክሉ ኮንጀኒታል ወይም የዕድገት ብልሽቶች ለማስተካከል የሚሰጡ በውሉ ላይ የተዘረዘሩ አገልግሎቶች እና ደጋፊ መዋቅሮች የጥርስ ሕክምናው አስፈላጊነት ከተረጋገጠ ራሳቸውን ላላቻሉ ሕፃናት ሲሰጡ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል። የ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም በጥርስ ሕክምና ዓይን ሲታይ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን እና ኦርቶግናቲክ ቀዶ ጥገናው የኮንጀኒታል ወይም የዕድገት ብልሽት ላለበት ዕድሜው ከ19 ዓመት በታች ለሆነ ተመዝጋቢ እንዲደረግ ፈቃድ ከሰጠ በውሉ ላይ በተጠቀሰው መሠረት ኦርቶግናቲክ ቀዶ ጥገና የመድን ሽፋን ይኖረዋል።

ክራውኖች፣ ካስቶች ወይም ሌላ ቀጥተኛ ያልሆኑ የተፈበረኩ ማስተካከያዎች በጥርስ ሕክምና አስፈላጊ ከሆኑ ብቻ እና በ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም አስፈላጊ እንደሆኑ እና የሚመከሩ ሆነው ሲገኙ የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል።

የመጀመሪያው የሩት ካናል ቴራፒው በ Willamette Dental Group ጥርስ ሐኪም የተጀመረ ከሆነ የሩት ካናል ቴራፒው ዳግመኛ ሕክምና ለመጀመሪያዎቹ 24 ወራት እንደ የመጀመሪያው ሕክምና አንድ አካል ተቆጥሮ የመድን ሽፋን ይኖረዋል። የመጀመሪያው የሩት ካናል ቴራፒው ተሳታፊ ባልሆነ አገልግሎት አቅራቢ ከተከናወነ፣ የዚህ ሩት ካናል ቴራፒው በ Willamette Dental Group ጥርስ ሐኪም ዳግመኛ ሕክምና ሲደረግለት ተገቢነት ያላቸው ጥምራ ክፍያ ግዴታዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

አጠቃላይ አንስቴዚያ በጥርስ ሕክምና ማዕከል ውስጥ የተከናወነ ከሆነ በውሉ ላይ በተጠቀሰው የጣምራ ክፍያ አከፋፈል አማካይነት የመድን ሽፋን ይኖረዋል፤ ይህ ሲሆን አገልግሎቱ የመድን ሽፋን ያለው ሲሆን እና የመድን ተመዝጋቢው ዕድሜው ከ7 ዓመት በታች ስለሆነ፣ የአካል ዕድገት ስንክልና ወይም አካለ ጉዳት ያለበት ስለሆነ በጥርስ ሕክምና ዓይን አንጻር ሲታይ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው።

በሕክምና አስፈላጊ ሆነው ከተገኙ፣ በ Willamette Dental Group የጥርስ ሐኪም በቅድሚያ በጽሑፍ ፈቃድ የተሰጠባቸው ከሆኑ፣ የሚሰጡት አገልግሎቶች በጥርስ ሕክምና ማዕከል ከሚሰጡት ሕክምናዎች ጋር ተመሳሳይ ሕክምናዎች ከሆኑ እና ተገቢነት ያላቸው የጣምራ ክፍያ ክፍያዎች ከተከፈሉ በሆስፒታል ውስጥ በጥርስ ሐኪም የሚሰጡ አገልግሎቶች የመድን ሽፋን ይኖራቸዋል።

ተጨማሪው ነገር ከተገጠመ 5 ዓመት ካለፈው እና የእርስዎን ጥቅማ ጥቅሞች ከፍ ያለ ደረጃ ለማድረስ ተጨማሪውን ነገር በሌላ መተካት በጥርስ ሕክምና ዓይን ሲታይ አስፈላጊ መሆኑ ከታመነበት ቀደም ሲል የነበረ ዴንቸር፣ ክራውን፣ ኢንሌይ፣ ወይም ሌላ ፕሮስቴቲክ ተጨማሪ ነገር የመድን ሽፋን ይኖረዋል።



Aetna IP_am-ET.indd 14 15/06/21 15:19

# የተለመዱ የኢንሹራንስ ልዩ ቃላት

የእርስዎን የኢንሹራንስ ፖሊሲ የበለጠ ለመረዳት አንዳንድ የተለመዱ የኢንሹራን ቃላትን ትርጓሜ ይማሩ።

### ጣምራ ኢንሹራንስ

ጣምራ-ኢንሹራንስ የእርስዎን ተቀናሽ (የእርስዎ የመድን ዕቅድ ያለው ከሆነ) ካሟሉ በኋላ ለሕክምና አገልግሎቶች እርስዎ የሚከፍሉት ገንዘብ መቶኛ ነው።

### ጣምራ ክፍያ

ጣምራ ክፍያ በዶክተር ለመታየት፣ ለድንገተኛ ሕክምና ክፍል ሕክምና እና ብዙውን ጊዜ በሐኪም ለሚታዘዙ መድኃኒቶች እርስዎ የሚከፍሉት ገንዘብ መጠን ነው። አንዳንድ የመድን ዕቅዶች ተቀናሾችን ከማሟላት ይልቅ ጣምራ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ያስገድድዎታል። ሌሎች የመድን ዕቅዶች ሁለቱንም እንዲያደርጉ ሊያስገድዱ ይችላሉ። የእርስዎ ጣምራ ክፍያዎች በተቀናሹ ገንዘብ መጠን ላይ ታሳቢ አይሆኑም ሆኖም ግን በእርስዎ ከኪስ ወጪ ተከፍሎ የሚደረግ ገንዘብ ገደብ ላይ የሚታሰቡ ይሆናሉ።

### ተቀናሽ

ተቀናሽ የእርስዎ የመድን ሽፋን ዕቅድ መክፈል ከመጀመሩ በፊት የመድን ሽፋን ላላቸው የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች የመድን ሽፋን ባለው ክፍለ ጊዜ (ብዙውን ጊዜ አንድ ዓመት) ወቅት እርስዎ የሚከፍሉት ገንዘብ ነው። ተቀናሹ በሁሉም አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚ ላይሆን ይችላል እና ሁሉም የመድን ዕቅዶችም ተቀናሽ የላቸውም። ለአንዳንድ የመድን ዕቅዶች፣ ተቀናሹ ከአውታረ መረብ ውጭ ላሉ አገልግሎቶች ብቻ ተፈጻሚ የሚሆን ነው።

### ብቁነት

በተከታታይ ለሁለት ወራት ለ 80 ሰዓታት በወር በትንሹ ከሠሩ በ SEIU 775 Benefits Group የጤና የመድን ሽፋን ለማግኘት ብቁ ነዎት። በእርስዎ የመድን ሽፋን ብቁ እንደሆኑ ለመቆየት፣ በወር 80 ሰዓታት መሥራትዎን መቀጠል መቻል አለብዎት።

### አውታረ መረብ ውስጥ ያለ እና ከአውታረ መረብ ውጭ ያለ ልዩነት

በአውታረ መረብ ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች በዝቅተኛ ወይም ያለ ምንም የጣምራ ክፍያ/ጣምራ ኢንሹራንስ ሊያገኙዋቸው የሚችሏቸው የእርስዎ የጤና መድን ዕቅድ ሽፋን የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ናቸው። ከአውታረ መረብ ውጭ ያሉ አገልግሎቶች አሁን በእርስዎ የመድን ዕቅድ የሚሸፈኑ ሆነው ሆኖም ግን ከአውታረ መረብ ውስጥ ካሉ አገልግሎቶች ይልቅ ከፍተኛ ጣምራ ክፍያ ወይም ጣምራ ኢንሹራንስ ሊኖራቸው ይችላል።

### የአባል መታወቂያ

የእርስዎ የአባል መታወቂያ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች እና ሠራተኞቻቸው የእርስዎን የመድን ሽፍን ትክክለኛነት እንዲያረጋግጡ እና ለአገልግሎቶቹ ክፍያን ማስተካከል እንዲችሉ የሚያግዛቸው ልዩ ከእርስዎ ጋር የተገናኘ ቁጥር ነው። በተጨማሪ የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች አንድን የተወሰነ አባል ፈልገው እንዲያገኙ እንዲሁም ስለ የእርስዎ የመድን ሽፋን ይገባኛል ጥያቄ እና ጥቅማ ጥቅሞች ሊኖርዎት የሚችሉ ጥያቄዎችን መልስ መስጠት የሚያስችላቸው ቁጥር ነው። የእርስዎ የአባል መታወቂያ ቁጥር በእርስዎ የአባል መታወቂያ ካርድ ላይ ሊገኝ ይችላል።

### አውታረ መረብ

የእርስዎ የጤና መድን ዕቅድ የእርስዎ የጤና መድን የጤና እንክብካቤ አገልግልቶችን እንዲያቀርቡ ከእነርሱ ጋር ውል ያለው አውታረ መረብ የተቋማት፣ የአገልግሎት ሰጪዎች (ዶክተሮች፣ ነርሶች) እና አቅራቢዎች ስብስብ ነው።

### ከኪስ የሚከፈል ገንዘብ ገደብ

ከኪስ የሚከፈል ገንዘብ ገደብ የእርስዎ የመድን ዕቅድ ለተቀረው የዓመቱ ክፍለ ጊዜ የመድን ሽፋን ላላቸው የጤና ወጪዎች 100% መክፈል ከመጀመሩ በፊት እርስዎ መክፈል ያለብዎት ገንዘብ መጠን ነው። በአጠቃላይ አነጋገር፣ ጣምራ ክፍያዎች፣ የእርስዎ ተቀናሽ፣ ጣምራ ኢንሹራንስ እና የመድን ሽፋን ያላቸው የአውታረ መረብ ውስጥ ክፍያዎች በዚህ ገደብ ላይ ታሳቢ ይሆናሉ።

### ተቀዳሚ የሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ወይም አገልግሎት ሰጪ (ዶክተር)

ተቀዳሚ የሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ለተከታታይ ሕክምና እርስዎን የሚያይዎት ዶክተር ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ነው። የእርስዎን ተቀዳሚ እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ በእርስዎ የጤና መድን ዕቅድ የድር ጣቢያ በኩል መምረጥ ይችላሉ። አንዳንድ የመድን ዕቅዶች በራስሰር ራሳቸው አንዱን ሊመድቡልዎት ይችሉ ይሆናል፣ ሆኖም ግን በማናቸውም ጊዜ ሊለውጡት ይችላሉ።

### ፕሪሚየም/ጣምራ ፕሪሚየም

ፕሪሚየም (ወይም ጣምራ ፕሪሚየም) በዶክተር ቢታዩ ወይም ባይታዩም በየወሩ ለጤና መድን ሽፋን እርስዎ የሚከፍሉት ገንዘብ መጠን ነው። በ SEIU 775 Benefits Group የመድን ሽፋን ያላቸው የእንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች መክፈል ያለባቸው ጣምራ ፕሪሚየም በወር $25 ነው።

### የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች እና የተኝቶ ታካሚ አገልግሎቶች

ተኝቶ ታካሚ አገልግሎት ለአንድ ሌሊትም ቢሆን በሆስፒታል ውስጥ እንዲያድሩ የሚያስገድድዎት ሕክምና ነው። አንዳንድ ምሳሌዎች ሕፃን መውለድ ወይም አንዳንድ የቀዶ ጥገና ሕክምናዎች ናቸው። የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎት ማናቸውም በሆስፒታል ውስጥ እንዲያድሩ የማያስገድድዎት የሕክምና አገልግሎት ነው።

### ይለፈኝ ማለት ወይም የይለፈኝ የመድን ሽፋን

በጤና መድን ሽፋን ሥር መመዝገብ የማይፈልጉ ከሆነ ወይም ያልዎትን የመድን ሽፋን እንዲቋረጥ ከፈለጉ (አስቀድመው ተመዝግበው ያሉ ከሆኑ)፣ በ ላይ የኦንላይን ቅጽ መሙሏት ወይም ወደ *My Plan* ወይም ወደ ደንበኛ አገልግሎት በመደወል የወረቀት ቅፅ እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይችላሉ። የመድን ሽፋንን ይለፈኝ ለማለት ከመረጡ፣ እስከ Open Enrollment 2022 (ዓመታዊ የምዝገባ ጊዜ ለጤና ሽፋን 2022) ድረስ ዳግመኛ መመዝገብ አይችሉም።



Aetna IP_am-ET.indd 15 15/06/21 15:19

SEIU 775
BENEFITS GROUP

ትምህርት – ጤና – ጡረታ መውጣት – ቅጥር ሥራዎች



ዳንኤል ኤም
እንክብካቤ ሰጪ፣ ሊንዉድ

## ምዝገባ ክፍት የሚሆነው፡- ጁላይ 1 – ጁላይ 20

በ *My Plan* ላይ ይመዝገቡ ወይም በእርስዎ የመድን ሽፋን ላይ ኦንላይን ለውጦችን ያድርጉ!

**myseiu.be/oe-myplan**

ጥያቄዎች አሉዎት?
እዚህ ላይ ይደውሉ፡-
**1-877-606-6705**

Aetna IP_am-ET.indd 16 15/06/21 15:19